
ህግህ ለእግሬ መብራት
የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት
ከዘፍጥረት - ዘዳግም
አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት
ክፍል አንድ
ከአድነው ተሾመ 1993 ዓ.ም

# ሕግህ ለእግሬ መብራት

ከአድነው ተሾመ

1993 ዓ.ም.

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም

(አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት)

## ክፍል አንድ

ይህንን መጽሐፍ ያ ደራሲው ፈቃድ በሙሉ
ወይም በከፊል ማባዛት ወይም መልሶ ማሳተም በሕግ
የተከለከለ ነው 1993 ዓ.ም

**Copyright 2001, Adnew Teshome**

# ምዕራፍ ሦስት

## <u>ዘጸአት</u>

(ጸአት) ማለት (መውጣት) ማለት ነው:: ይህ መጽሐፍ የእስራኤላውያንን ከግብጽ ባርነት ነፃ መውጣትና፣ ነፃ ከወጡም በኋላ የነበረባቸውን ፈተናና ትግል፣ እንዲሁም ከሲና ተራራ የተሰጣቸውን ሕግና የመገናኛውን ድንኳን መሠራት የሚተርክ መጽሐፍ ነው::

እስራኤላውያን፤ ማለትም የአብርሃም፣ የይስሐቅ እና የያዕቆብ (የእስራኤል) ልጆች እንዴት <u>ከአንድ ቤተሰብ ወደ አንድ ሕዝብ</u> እንደተለወጡና እንደበዙ የሚያሳይ መጽሐፍ ነው:: ዘፍጥረት የቤተሰብ ታሪክ (የአዳም፣ የኖኅ፣ የአብርሃም) ሲሆን፤ ዘጸአት ግን የአንድ ብሔር (የእስራኤላውያን) ታሪክ ነው:: ዘፍጥረትንና ዘጸአትን የምታገናኘው ጥቅስ ዘፍ. 12፡2 ናት:: «<u>ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ</u>፣ እባርክሃለሁ ስምህንም አከብረዋለሁ::» ይህ ለአብርሃም የተሰጠ የተስፋ ቃል ነው::

እንደ ሌሎቹ የኦሪት መጻሕፍት ዘጸአትም በሙሴ እንደ ተጻፈ ይታመናል::

በዚህ መጽሐፍ (በዘጸአት) ውስጥ የምናነበው የእስራኤላውያን ከባርነት ነጻ መውጣት ታሪክ፣ በአዲስ ኪዳን በክርስቶስ ኢየሱስ ደም በኩል የሚገኘውን ከኃጢአት ባርነት ነጻ የመውጣት ምሳሌ ሆኖ እናገኘዋለን::

«በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻ አወጣን፤ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ አንደገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ» (ገላ. 5፡1)::

- ዘፍጥረት <u>የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት</u> ሲያሳይ፣ ዘጸአት ደግሞ <u>የእግዚአብሔርን ኃይል</u> ያሳያል:: ይህ መጽሐፍ በሦስት ይከፈላል::

I. ከግብጽ ባርነት ነጻ መውጣት (ከምዕ.1-18)
II. የሕጉ መሰጠት (ከምዕ. 19-24)
III. የመገናኛው ድንኳን (ከምዕ. 25-40)

እነዚህ ሦስት ክፍሎች፤

- ነጻነትን -- ከባርነት ነጻ መውጣት
- ኃላፊነትን -- የሚመሩበት ሕግ ተሰጣቸው
- በረከት(ኅብረትን ያመለክታሉ (ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበት የመገናኛ ድንኳን ተተከለ)፡፡

ነጻነት ያለ ህግ (ያለ ኃላፊነት ያለ ተጠያቂነት) ልቅነት ነው፡፡ ኃላፊነት ያለ ነጻነት እሥራት ነው፡፡ ነጻነትና ኃላፊነት ደግሞ ያለ በረከት ትርጉም አይኖራቸውም፡፡ በረከቱ ኃላፊነትን የመወጣት ውጤት ነው፡፡

## I. ከግብጽ ባርነት ነጻ መውጣት፤ ምዕ. 1-18

ሀ. የባርነቱ መንሥኤ፡ - የእስራኤላውያን በግብጽ ምድር መብዛትና መበርታት ነው (ዘጸ. 1፡1-22)፡፡
ለ. የነፃ አውጪው (የሙሴ) መዘጋጀትና ጥሪ፤

1. በግብጽ ውስጥ (ምዕ. 2፡1-15) 40 ዓመት
2. በምድያም ምድረ በዳ (ምዕ. 2፡16-25) 40 ዓመት
3. የእግዚአብሔር ጥሪ ለሙሴ (ምዕ.3እና4) ለሚቀጥሉት 40 ዓመታት ሕዝቡን ለመምራት፡፡

D.L. Moody የሚባል የታወቀ ሰባኪ ስለ ሙሴ እንዲህ አለ፤

.ሙሴ ለአርባ ዓመታት በግብጽ «አለሁ» እያለ ኖረ፣
.ለሚቀጥሉት አርባ ዓመታት ባዶነቱን ተማረ፤
.ለመጨረሻው አርባ ዓመታት እግዚአብሔር በባዶ ሰው ምን ያህል ኃይሉንና ክብሩን መግለጥ እንደሚችል አየ፡፡

ሐ. የፈርዖን እግዚአብሔርን መገዳደር (ምዕ. 5-11)

በዚህ ክፍል እግዚአብሔር በግብጽ ላይ ያመጣውን 10 መቅሠፍቶች እናያለን፡፡

የፈርዖን ልቡን ማደንደን የእግዚአብሔር ኃይል በዓለም ላሉ ሁሉ እንዲገለጥ ምክንያት ሆነ፡፡

ከዚህ ክፍል የምንማረው፤ እግዚአብሔር በከባድ የሚያሳልፈንና ጠላትም የአቅሙን ያህል እንዲገዳደር የሚፈቅድለት ያን ያህል ክብሩንና ኃይሉን ለጠላት፥ ለእኛም ሆነ ለሰዎች ሁሉ ለመግለጽ ብሎ እንደሆነ ነው።

መ. በእግዚአብሔር ኃይል ከግብጽ ነፃ ሲወጡ (ምዕ. 12-18)

1. የፋሲካ ደም መርጨትና ስርዓት (ምዕ. 12፡1፤ ምዕ. 13፡16) በኢየሱስ ክርስቶስ ደም መፍሰስ ያገኘው ነፃነት ምልክት ነበረ። «ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶአልና» (1ቆሮ. 5፡7)።

.ለእያንዳንዱ ቤተሰብ አንድ ጠቦት ታርዶ ደሙ በቤቱ መቃንና ጉበን ተቀባ። የሞት መልአክ የግብፃውያንን በኩር ሁሉ ለመግደል (10ኛው መቅሠፍት) በግብጽ ላይ በሚያልፍበት ጊዜ በእስራኤላውያን በር ላይ ደሙን ሲያይ ያንን ቤት ያልፈው ነበር። የኢየሱስ ክርስቶስ ደምም በእኛ ላይ እንደዚህ ነው የሚሠራው።

2. የእስራኤላውያን ከግብጽ ወጥቶ ወደ ቀይ ባህር መጓዝ (13፡17-22)፤ እስራኤላውያን ከግብጽ በወጡ ጊዜ ሕጻናትና ሴቶች ሳይቆጠሩ (600,000 ስድስት መቶ ሺህ) ወንዶች ነበሩ በአጠቃላይ (3,000, 000 ሦስት ሚሊዮን) ያህል ሕዝብ እንደነበረ ይገመታል። (ዘጸ. 12፡37)፤

3. በቀይ ባሕር መካከል ማለፍ (ዘጸ.14፥1-31)

ሀ. ፈርዖን እሥራኤላውያን እስከ ቀይ ባህር ማሳደድ (ዘጸ 14፡1-12)

ይህ ክፍል የሚያሳየን ሰይጣን ከኃጢአት ባርነት ነፃ ከወጣን በኋላም እንኳን ተስፋ እንደማይቆርጥ ነው። እንደገና በባርነት ቀንበር ሊይዘን ይፈልጋል። እሥራኤላውያን ፈርዖንን ባዩ ጊዜ ፈርተው «ብንገዛላቸው ይሻላል» (14፡12) ሲሉ እንሰማለን።

ለ. የእሥራኤላውያን መዳን የግብጻውያን መስጠም (ምዕ. 14፡13-ምዕ. 15፡21)

4. ከቀይ ባህር ወደ ሲና ተራራ ጉዞ (ምዕ. 15፡22-18፡27)

ሀ. ከቀይ ባህር ወደ ምድረ በዳ ጉዞ (15፡22-ምዕ. 17፡1)

የእስራኤላውያን በምድረ በዳ ማጉረምረም (ምዕ. 15፡11-16-9)

ከሦስት ቀን በፊት (15፡22) ለእግዚአብሔር ሲዘምሩና ሲጨፍሩ የነበሩት ሰዎች በምድረ በዳ ሲያጉረመርሙ እናያለን።

ማጉረምረም- በቀይ ባህር ወዲህ ማዶ ፈርዖን ሲመጣባቸው «ለግብጻውያን ብንገዛ ይሻል ነበር» አለ (14፡11-12)

።

ምሥጋና- እግዚአብሔር ቀይ ባህርን ከፍሎ ሲያሻግራቸውና ጠላቶቻቸው ሁሉ በባህር ተንሳፈው ሲያዩ መዘመርና ማመስገን ጀመሩ (ምዕ. 15፡1-21)። የጠላቶቹን ሬሳ እያየ ማመስገን ማን ያቅተዋል? እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው ግን ከቀይ ባህር ወዲህ ማዶ ሆነን እግዚአብሔር አይተወንም ለጠላቶቻችን አሳልፎ አይሰጠንም ብለን በእምነት ስናመሰግነው ነው። ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልምና (ዕብ. 11÷6)።

ማጉረምረም ከዘመሩና ካመሰገኑ ከሦስት ቀን በኋላ በምድረ በዳ የሚጠጡት ጥሩ ውኃ ሲያጡ «ምን እንጠጣለን» ብለው አጉረመረሙ። የማራ ውኃ መራራ ነበርና (ምዕ. 15፡22)።

ማጉረምረም- በምዕ. 16፡1-2 «በራብ ልትገሉን ነው» ብለው አንጎራጎሩ።

ለ. ከምድረ በዳ ወደ ሲና ተራራ ጉዞ (ምዕ. 17፡1-18፡27)

በዚህ ክፍል እስራኤላውያን እንደገና «የምንጠጣውን ውሃ ስጠን» ብለው ሙሴን ሲጣሉት እናያለን (17፡1-4) እግዚአብሔር ግን በምህረቱ ከዓለቱ ውሃ አፈለቀላቸው (17፡5-7)

ለእኛም «አታንጐራጉሩ» የሚል ማስጠንቀቂያ አለን «ከእነርሱም አንዳንዶቹ እንዳንጐራጐሩ በሚያጠፋው እንደ ጠፉ አታንጐራጉሩ» (1ቆሮ. 10፡10)።

ከግብጽ ነጻ በመውጣት ታሪክ ውስጥ የምናያቸው ምሳሌዎች

ግብጽ፡ - የዓለም ምሳሌ- (በዓለም ውስጥ የኃጢአት ባርነት አለ) «ከግብጽም ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስቶስ መነቀፍ እጅግ የሚበልጥ ባለጠግነት እንዲሆን አስቦአልና ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኘው ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራን መቀበልን መረጠ (ዕብ. 11፡25-26)፡፡

ግብጽን፡ - በኃጢአት ከሚገኝ ጊዜያዊ ደስታ ጋር ያወዳድራል፡፡

ፈርዖን፡ - የዚህ ዓለም ገዢ የሆነው የሰይጣን ምሳሌ፡ - ፈርዖን የግብጽ ገዠ እንደነበረ፡፡

ቀይ ባህር፡ - የደኅንነትና የጥምቀት ምሳሌ (1ቆሮ. 10፡1-2)

ዓለቱ፡ - (ዘጸ. 17፡5-7) የክርስቶስ ምሳሌ ነው (1ቆሮ. 10፡4 ዮሐ. 7፡37) «ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ»

ሙሴ፡ - የክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡

«... የሃይማኖታችንን ሐዋርያና ሊቀካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ፤ ሙሴ ደግሞ በቤቱ ሁሉ የታመነ እንደሆነ እርሱ (ክርስቶስ) ለሾመው የታመነ ነበር» (ዕብ. 3፡1-2)፡፡

ይህ ክፍል በሦስት ይከፈላል፡፡

## II. የሕጉ መሰጠት ምዕ. 19-24

ይህ ክፍል በሦስት ይከፈላል፡፡

፩. ምግባራዊ ሕግ- አሥርቱ ቃላትን ያጠቃልላል (ምዕ. 19-20)
፪. ማኅበራዊ ሕግ (ምዕ. 21-23)
፫. ሃይማኖታዊ ሕግ (ከምዕ. 24 ጀምሮ ዘሌዋውያንንም ያጠቃልላል)

### ሕጉ የተሰጠበት ምክንያቶች

#### ሀ. የጽድቅ መለኪያ እንዲሆን፤

የአብርሃም ዘሮች በቤተሰብ ደረጃ በነበሩበት ጊዜ (እስከ ዘፍጥረት መጨረሻ) እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባው ቃል ኪዳን በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ነበር፡፡ በዘጸአት ግን

እስራኤል ወደ ብሔርነት ሲለወጥ ቋሚ የሆነ የተጻፈ ሕግ አስፈለጋቸው ያም ሕግ እግዚአብሔር ከእነርሱ የሚጠብቀውን የጽድቅ ህይወት ያመለክታል።

ለ. የሰውን ኃጢአተኛነት አጉልቶ እንዲያሳይ፡ -

ሮሜ 3፡20 «ኃጢአት በሕግ ይታወቃልና።»
ሮሜ 7፡7 «በሕግ ባይሆን ኃጢአትን ባላወቅሁም ነበር። ሕጉ፡ - አትመኝ ባላለ ምኞትን ባላወቅሁም ነበርና።»

ሕግ ለሰዎች እንደ መንፈሳዊ መስታወት ሆኖ ነበር የተሰጠው። ማንነታቸውን አይተውበት የእግዚአብሔርን ምህረቱ እንዲፈልጉ እንጂ የተሰጠውን ሕግ መፈጸም ስለሚችሉ አልነበረም።

ገላ. 3፡19 «ታዲያ ሕግ የተሰጠው ለምንድነው? ... ክፉ ሥራ ምን መሆኑን ለማመልከት ነው...» የ1980 እትም።

ሐ. የእግዚአብሔርን ቅድስና ለመግለጽ «ሕጉ ቅዱስ ነው ትእዛዚቱም ቅድስትና ጻድቅ በጎም ናትና ሮሜ 7፡12።

የእግዚአብሔርን ቅድስና አውቀው በእግዚአብሔር ፍርሃት እንዲመላለሱ።

<u>የብሉይ ኪዳን ሕግና የአዲስ ኪዳን ጸጋ ልዩነት፤</u>
<u>(ሕግና ጸጋ)</u>

1. በብሉይ ኪዳን ሰው የሚጸድቀው ሕጉን በመጠበቅ ነበረ። በአዲስ ኪዳን ግን ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ሆነልን። «የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ክርስቶስ የህግ ፍጻሜ ነውና» (ሮሜ 10÷4)።
   - «ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበርና ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ» (ዮሐ. 1÷17)።
   - «ነገር ግን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ <u>በሕግ ሥራ ስለማይጸድቅ</u> እኛ ራሳችን በሕግ ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንጸድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል። (ገላ. 2÷16)።
   - ሕጉ የሚናገረው (በተለይ የሥነ ምግባር ሕግ) የምንፈጽመው ለመጽድቅ ሳይሆን፣ በክርስቶስ አምነን ስለ ጻደቅን መሆን

አለበት በኤፌ. 2÷9 እና 10 «<u>ሥራ</u>» የሚለውን ቃል ተመልከት፡፡ በቁ. 9 «ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም» ሲል የዳንነው እኛ በሠራነው ሥራ (ሕግን በመጠበቃችን) አይደለም ማለቱ ነው፡፡ በቁ. 10 ላይ ደግሞ «መልካሙን <u>ሥራ</u> ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን» ሲል ዳግመኛ ከተወለድን በኋላ (አዲስ ፍጥረት ከሆንን በኋላ (ሥራ) እንደሚጠበቅብን ያሳያል፡፡

- በያዕቆብም ውስጥ «ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው» ያዕ. 2÷26 የሚለው፣ በእምነት ከጸደቅን <u>በኋላ</u>፣ እውነተኛ እምነት እንዳለን የሚታወቀው በምንሠራው ሥራ እንደሆነ ሲገልጽ ነው፡፡

2. <u>በብሉይ ኪዳን ይደረጉ የነበሩት (ሥርዓቶች) በክርስቶስ ፍጻሜ ስላገኙ ተሽረዋል</u>፡፡

- ቆላ. 2÷16-23 «.. እነዚህ ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ናቸውና አካሉ ግን የክርስቶስ ነው፡፡»
- ዕብ. 9÷12-14፤ የእንስሳት ደም በክርስቶስ ደም እንደተተካ
- ዕብ. 10÷1-18፤ በሕጉ ይቀርቡ የነበሩት መስዋዕቶች ሁሉ በክርስቶስ ዘላለማዊና ፍጹም መስዋዕትነት እንደተሻሩ ያሳየናል፡፡

3. እግዚአብሔር ሰዎችን የሚገናኝበት መንገድ ሕግ መሆኑ ቀርቶ ጸጋ ሆኗል፡፡ ከሕግ ኪዳን ወደ ጸጋ ኪዳን ተሸጋግረናል (ከዓመተ ፍዳ ወደ ዓመተ ምህረት)፡፡
   - 2ቆሮ. 3÷6 «እርሱም ደግሞ በመንፈስ እንጂ በፊደል በማይሆን ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃን ፊደል ይገድላልና መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል፡፡»

ሕጉ - ፊደል ነው- ይገድላል
ጸጋ- መንፈስ ነው -ሕይወትን ይሰጣል፡፡

- ሮሜ 8÷2-4 «በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና፡፡ ከሥጋ የተነሣ ስለደከመ ለሕግ ያልተቻለውን፣ እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ በኃጢአትም ምክንያት ልኮ አድርጓልና እንደ መንፈስ ፈቃድ አንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ በማንመላለስ በእኛ የሕግ ትእዛዝ ይፈጽም ዘንድ ኃጢአትን በሥጋ ኰነነ፡፡»

ሕግ፡ - ኃጢአትና ሞትን አመጣ፡፡
ጸጋ፡ - ሕይወትንና አርነትን አመጣ፡፡

## ፩፥ ምግባራዊ ሕግ - አሥርቱ ቃላት ዘጸ. 20፥1-17

ከ1-4 ያሉት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ግንኙት ሲያመለክቱ፣ ከ5-10 ያሉት ደግሞ በሰውና በሰው መካከል ያለውን ግንኙነት ያመለክታሉ፡፡

1. «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» (ቁ. 3)

1ዮሐ. 5፥21 «ልጆች ሆይ ከጣዖታት ራሳችሁን ጠብቁ»

2. «ከላይ በሰማይ ካለው፣ በታችም በምድር ካለው፣ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ፡፡ አትስገድላቸው፡ አታምልካቸውምም» ቁ. 4-5

ዮሐ. 4፥24 «እግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚሰግዱለትና (የሚያመልኩትም) በእውነትና በመንፈስ ሊሰግዱለት (ሊያመልኩት) ይገባል፡፡»

3. «የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነፃውምና» ቁ. 7

ሐዋ.19፥13-17፣ የኢየሱስን ስም በከንቱ ስለጠሩ ሰዎች ይናገራል፡፡

4. «የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ፡፡ ስድስት ቀን ሥራ ተግባርህንም ሁሉ አድርግ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ሰንበት ነው» ቁ. 8-10፡፡

«እኛስ ያመንን ወደ ዕረፍቱ እንገባለን» (ዕብ. 4፥3-10) በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔር ለአማኞች ዕረፍትን እንዳዘጋጀላቸው ይናገራል እንጂ እንደ ብሉይ ኪዳን ለሰንበት ሥርአት ተገዙ አይልም (ማቴ. 12፥8፣ ማር. 2፥27-28፣ ቆላ. 2፥16-17) ፡፡

5. አባትህንና እናትህን አክብር፤ እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም (ቁ. 12) -- ኤፌ. 6÷1-3

6. አትግደል -- ቁ. 13

ሮሜ 13÷8-10 ከአስርቱ ቃላት ውስጥ ከ6-10 ያሉትን ያጠ ቃልላል።

7. አታመንዝር ቁ. 14 -- ማቴ. 5÷21-30
8. አትስረቅ ቁ. 15 -- ኤፌ. 4÷28
9. በሐሰት አትመስክር ቁ. 16 -- ኤፌ. 4÷25
10. የባልንጀራህ የሆነው ማናቸውንም ነገር አትመኝ ቁ. 17

ያዕ.1÷14-15 «ምኞት ጸንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች»

በአዲስ ኪዳን የተሰጠን <u>አንድ የፍቅር ትእዛዝ</u> አሥርቱን ቃላት ሁሉ ያጠቃልላል ዮሐ. 13÷34፤ ማቴ. 22÷38-40፤ ሮሜ 13÷8-10

## ፪÷ <u>ማኅበራዊ ሕግ</u>(ምዕ. 21-23)

1. በጌታና በባሪያ መካከል (ምዕ. 21÷1-11)
2. ሰው ሰውን በአካል ወይም በቃል ከበደለ ምን እንደሚሆን (21÷12-36)
3. ንብረትን በሚመለከት (ምዕ. 22÷1-15)
4. አንዳንድ ርኩሰትና ክፉ አድራጎትን በሚመለከት (ምዕ. 22÷16-31)
5. ፍትሕንና ፍርድን በሚመለከት (ምዕ. 23÷1-9)
6. ስለሰንበትና በዓላት (ምዕ. 23÷10-19)
7. ከሌሎች አህዛብ ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙት (23÷20-33)

## ፫÷ <u>ሃይማኖታዊ ሥርዓት (ሕግ)</u> (ምዕ. 24) 24÷4-8

«ሙሴም የእግዚአብሔርን ቃሎች ጻፈ ማለዳም ተነሣ፣ ከተራራውም በታች መሠዊያን÷ አሥራ ሁለትም ሐውልቶች ለአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ሠራ። የሚቃጠል መሥዋዕት እንዲያቀርቡ ለእግዚአብሔርም ስለ ደኅንነት መሥዋዕት በሬዎችን እንዲሠዉ የእስራኤልን ልጆች ጐበዛዝት ሰደደ። ...

የደሙንም እኩሌታ ወስዶ በቆሬ ውስጥ አደረገው የደሙንም እኩሌታ በመሠዊያው ረጨው። የቃል ኪዳኑንም መጽሐፍ ወስዶ ለሕዝቡ አነበበላቸው። ... ሙሴም ደሙን ወስዶ በሕዝቡ ላይ ረጨው። ... እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ያደረገው የቃል ኪዳኑ ደም እነሆ አለ።»

ሃይማኖታዊ ሥርዓት በምዕ. 24 ቢጀመርም በሚቀጥሉት ምዕራፎችና በኦሪት ዘሌዋውያንም ውስጥ ሃይማኖታዊው ሕግ ይቀጥላል።

III የመገናኛው ድንኳን (ምዕ.25-40

ሀ. የአሠራሩ መዋቅር ሲሰጥ (25-31)
ለ. ሥራው ሲስተጓጐል (ምዕ. 32-34)
ሐ. ሥራው ሲፈጸም (ምዕ. 35-40)

እግዚአብሔር ለሙሴ የመገናኛውን ድንኳን እንዲሠራ በተራራ ላይ መመሪያ ሲሰጠው በተደጋጋሚ፡ -

«በተራራው ላይ እንዳሳየሁህ ምሳሌ እንድትሠራ ተጠንቀቅ።» ሲለው እናነባለን (ዘጸ. 25፥40፤30፤27፥8፤ ሐዋ. 7፥44፤ ዕብ. 8፥5) እኛም ለእግዚአብሔር የምንሠራለት ነገር ሁሉ ልክ እርሱ በነገረንና ባሳየን መንገድ ተጠንቅቀን መሆን እንዳለበት ያሳስበናል። «አገልግሎትህን ትፈጽመው ዘንድ ተጠንቀቅ» ቆላ. 4፥17።

## የመገናኛው ድንኳን በሦስት ይከፈላል

1. የማደሪያው አደባባይ
2. ቅድስት
3. ቅድስተ ቅዱሳን

የድንኳኑ ወርድ 50 ክንድ ሲሆን ርዝመቱ ደግሞ 100 ክንድ ነበረ ዙሪያውን 100+100+50+50=300 ክንድ ነበረ። በርዝመቱ በኩል 20 ምሰሶዎች ሲኖሩ በወርዱ በኩል ደግሞ 10 ምሰሶዎች ነበሩ በአጠቃላይ ዙሪያውን 60 ምሰሶዎች ነበሩት። በምሰሶዎች መካከል ያለው ሥፍራ በሙሉ የሚሸፍኑ መጋረጃዎች ነበሩ።




የመገናኛው ድንኳን ወርድና ርዝመት

ቅድስት የተባለው ክፍል 20 ክንድ በ10 ክንድ ሲሆን ከውጪው አደባባይ ቅድስት ወደተባለው ክፍል የሚያሳልፍ መጋረጃ ነበረ፡፡

ቅድስተ ቅዱሳን የተባለው ክፍል ደግሞ ቅድስት ከተባለው ክፍል የሚቀጥል ሆኖ 10 ክንድ በ10 ክንድ ሆኖ የተሠራ ነበረ፡፡

- በሰሎሞን ጊዜ የተሠራውን መቅደስም ስንመለከት በመቅደሱ ውስጠኛ ክፍል የነበረው ቅድስተ ቅዱሳን 20 ክንድ በ20 ክንድ /Square/ እንደነበረ እናነባለን (1ነገ. 1፥20) ፡፡ በዮሐንስ ራዕይ ላይ ደግሞ አዲሲቷን ኢየሩሳሌም በምናይበት ጊዜ የከተማይቱ ርዝመት፣ ስፋትና፣ ከፍታ እኩል (Cube) እንደሆነ እናነባለን፡፡ (ራዕ. 21፡16)

ይህ አሠራር (Cube) የፍጹምነት ምልክት እንደሆነ እናያለን፡፡ ማንኛውም እስራኤላዊ ወደ አደባባዩ መግባት ሲችል፤ ወደ ቅድስት መግባት የሚችሉ ግን ካህናት ብቻ ነበሩ፡፡ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን መግባት የሚችለው ደግሞ ሊቀ ካህኑ ብቻ ነበረ፡፡ እርሱም ልዩ ዝግጅት ካደረገ በኋላ በዓመት አንድ ጊዜ የራሱንና የሕዝቡን ኃጢአት የሚያስተሰርይ ደም ይዞ ይገባል (ዕብ. 8፥7)፡፡

የመገናኛው ድንኳን፤ ከሰው አፈጣጠር ጋር ያለው ግንኙነት፡-
የውጪኛው ክፍል፡ - ሥጋ- የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ነው
(1ቆሮ. 6፥19-20)፡፡

ቅድስት፡ - ነፍስ- «በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ» በሥጋና
በመንፈስ መካከል ያለ ክፍል (ሮሜ 12፥2)

ቅድስተ ቅዱሳን መንፈስ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት የምናደርግበት ክፍል ነው» (ዮሐ. 4÷24)::

እግዚአብሔር በአዲስ ኪዳን ሰውን የራሱ ማደሪያ እንዲሆን እንደመረጠ እናያለን:: እግዚአብሔር የሚያድርበት ቅድስተ ቅዱሳን መንፈሳችን» ነው::

የእግዚአብሔር ቃል «ሥጋችን» የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆነ ይነግረናል (1ቆሮ. 6÷19):: በሥጋችን ውስጥ ያለው መንፈሳችን (ልባችን) ደግሞ የእርሱ ማደሪያ (ቅድስተ ቅዱሳን) ነው::

«እግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚያመልኩትም በእውነትና በመንፈስ ሊያመልኩት ይገባል» (ዮሐ. 4÷24)::

## <u>በመገናኛው ድንኳን የነበሩ ዕቃዎች</u>

ዕብ. 9፡ 1−5 ዘጸ. 25-31




በውጭኛው ክፍል፡ - የናስ መሠዊያ እና የመታጠቢያ ሰን (ሳህን)

በቅድስት፡ - የኅብስት ገበታ፣ የወርቅ መቅረዝና የዕጣን መሰዊያ

በቅድስተ ቅዱሳን፡ - ታቦቱና የሥርየቱ መክደኛ

በአጠቃላይ ሰባት ዕቃዎች ናቸው::

<u>የሰባቱ ዕቃዎች ምሳሌነት</u>

1. <u>የናሱ መሠዊያ</u>: - (ዘጸ. 27፡1-8፤ 29፡10-14፤ 38፡1-7)

ይህ መሠዊያ እስራኤላውያን ለኃጢአታቸው ሥርየት የሚሆንን የእንስሳ መስዋዕት ይዘው ለካህኑ የሚያቀርቡበትና ካህኑ የደም መሥዋዕት አድርጎ እንስሳውን በመሠዊያው ላይ የሚቃጠልበት መሠዊያ ነው:: ይህም ለኃጢአታችን ሥርየት ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰዋበትን መስቀል ያመለክታል:: ቃሉ፤ «ደም ሳይፈስ ስርየት የለም» እንደሚለው ሁሉ የደም መሥዋዕት የሚቀርብበት ሥፍራ ነው::

ይህ የሚያመለክተው ስለ ኃጢአታችን ስርየት የእግዚአብሔር በግ ሆኖ ስለተሰዋልን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መስዋዕትነት ነው:: «እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፣ በመረቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት <u>በኢየሱስ ደም</u> በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል <u>እንድንገባ ድፍረት አለን</u>» (ዕብ. 10፥19)::

«የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል 1ዮሐ. 1፥7::

2. <u>የመታጠቢያው ሰን (ሳህን)</u>: - (ዘጸ. 30፡17-21፤ 38፣8) ይህ ዕቃ ካህናት ለማገልገል ወደ መገናኛው ድንኳን ሲገቡ ምንም ዓይነት አገልግሎት ከመስጠታቸው በፊት እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን የሚታጠቡበትን ውሃ የሚይዝ ነው:: ይህም በመንፈስ ቅዱስና በቃሉ መታጠብን (መታደስን) ያሳስበናል::

«እንደ ምሕረቱ መጠን <u>ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብ በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን</u> እንጂ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለነበረው ሥራ አይደለም» (ቲቶ 3፡5)::

መንፈስ ቅዱስ እኛን ለማደስ የሚጠቀምበት ውሃ ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል ነው:: «በውሃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ» (ኤፌ. 5፡26)::

ይህ የመታጠቢያ ሳህን ለእኛ የሚሰጠው ትምህርት ቢኖር: - ማንኛውንም አገልግሎት ከመስጠታችን በፊት ራሳችን በቃሉ ውኃና በመንፈስ ቅዱስ መታጠብ እንዳለብን ነው::

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁለት ዕቃዎች በማደሪያው አደባባይ የነበሩ ናቸው።

3. <u>የኅብስት ገበታ</u>፡ - (ዘጸ. 25፥23-30፤ 37፣ 10-16)
ይህ የኅብስት ገበታ፣ በቅድስት ውስጥ የሚገኝ፣ ካህናት ብቻ ሊበሉት የሚችሉትን ኅብስት የሚይዝ ገበታ ነበረ። (1ሳሙ. 21፡4-6፣ ማቴ. 12፥3-4)
ይህ የኅብስት ገበታ የኢየሱስ ክርስቶስን የሕይወት እንጀራነት የሚያሳስብ ነው። «የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፣ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምን ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም» (ዮሐ. 6፥35)።
«ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም» (ማቴ.4፥4)።

4. <u>የወርቅ መቅረዝ</u>፡ -(ዘጸ. 25፥31-40 27፥20-21፤ 37፥17-24)
ይህ የወርቅ መቅረዝ በቅደስቱ ውስጥ ካሉት ሦስት ዕቃዎች ሁለተኛው ነበረ። ተግባሩም፣ ዘወትር ያለማቋረጥ ዘይት ተጨምሮበት ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ፊት እንዲያበራ ነበር።

የመንፈስ ቅዱስ ዘይት በውስጣችን ሞልቶ ዘወትር መብራታችን በእግዚአብሔር ፊት መብራት እንዳለበት ያስታውሰናል። «ወገባችሁ የታጠቀ፣ መብራታችሁ የበራ ይሁን» (ሉቃ. 12፡35)። «እናንተ የዓለም ብርሃን (ማቴ. 5፡14-16)።

. ዘይታቸው ከማሰሮ ውስጥ ጎደሎ እንደነበረ እንደ አምስቱ ሰነፍ ቆነጃጅት እንዳንሆን (ማቴ. 25፡1-13)።
ከሁሉ በላይ የዚህ የወርቅ መቅረዝ ምሳሌነት እውነተኛ ብርሃን የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው። «ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛ ብርሃን ወደ ዓለም ይመጣ ነበር» (ዮሐ. 1፥9)
«እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም» (ዮሐ. 8፥12)።

5. <u>የዕጣን መሠዊያ</u>፡ - (ዘጸ.30፡1-10፤ 37፡25-28)

ይህ የዕጣን መሠዊያ በቅድስት ውስጥ ያለው ሦስተኛው ዕቃ ነበረ። ልክ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን መግቢያው ላይ ያለ ዕቃ ነበረ። ዕጣን በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ <u>የቅዱሳን ጸሎት</u> ምሳሌ ነው።

ራዕ. 5፡8 «... እያንዳንቸውም በገናንና የቅዱሳን ጸሎት የሆነ ዕጣን የሞላበትን የወርቅ ዕቃ ያዙ።»

ራዕ. 8፡3-4 «ሌላም መልአክ መጣና የወርቅ ጥና ይዞ በመሠዊያው አጠገብ ቆመ፤ በዙፋኑም ፊት ቆመ በዙፋኑም ፊት ባለው በወርቅ መሠዊያ ላይ ለቅዱሳን ሁሉ ጸሎት እንዲጨምረው ብዙ ዕጣን ተሰጠው። የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ።»

ሐዋ. 10፡4 «... ጸሎትህና ምጽዋትህ በእግዚአብሔር ፊት ለመታሰቢያ እንዲሆን ዐረገ ።»
መዝ. 140፡2 «ጸሎቴን በፊትህ እንደ ዕጣን ተቀበልልኝ ።»
ይህ የዕጣን መሠዊያ በተለይ «በኢየሱስ ክርስቶስ» ስም ለእግዚአብሔር የምናቀርበውን የምልጃና የምሥጋና ጸሎት ያሳስበናል።
ዕብ. 13፡15 «እንግዲህ ዘወትር ለእግዚአብሔር የምስጋና መሥዋዕት ማለት ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮችን ፍሬ በእርሱ እናቅርብለት።»

6. የኪዳኑ ታቦት፡ - (ዘጸ. 25፡10-16፣ 37፡1-5፤ ዕብ.9፡4) ይህ የኪዳን ታቦት በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ከሚገኙት ሁለት ዕቃዎች አንደኛው ነበረ። ይህ የኪዳን ታቦት የሚያመለክተው እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ነው፡፡ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የገባውን ቃል ኪዳን በእርሱ በኩል በታማኝነት እንደሚጠብቅ ማረጋገጫ ነበረ። በክርስቶስ ደም በኩል የሆነልንን አዲስ ኪዳንም የሚያሳስብ ነው (1ቆሮ. 11፡25)።

በኪዳኑ ታቦት ውስጥ የነበሩት ሦስት ነገሮች፣ ዕብ. 9፡4

ሀ. የኪዳኑ ጽላት (ዘጸ. 25፡16) «በታቦቱ ውስጥ እኔ የምሰጥህን ምስክር ታስቀምጣለህ ይህ አሥርቱ ቃላት የተጻፈበት ጽላት ነበረ፡፡ ጽላቱ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ሕግ ወይም የእግዚአብሔርን ቃል ሲሆን፤ በአዲስ ኪዳን ያለው ምሳሌነት፤ ጽላቱ የአማኞች ልብ ሲሆን፣ በጽላቱ ላይ ያለው ቃል ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል እና የእግዚአብሔር ቃል የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ነው።

ዕብ.8፡10 «... ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፤ በልባቸውም እጽፈዋለሁ፣ እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ። እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል።»

ዕብ. 10፡16 «ከዚያ ወራት በኋላ ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው፤ ይላል ጌታ በልባቸው ሕጌን አኖራለሁ በልቡናቸውም እጽፈዋለሁ።»

2ቆሮ. 3፣3 «እናንተም በሕያው እግዚአብሔር መንፈስ እንጂ በቀለም አይደለም፣ ሥጋ በሆነ በልብ ጽላት እንጂ በድንጋይ ጽላት ያልተጻፈ በእኛም የተገለገለ የክርስቶስ መልእክት እንደ ሆናችሁ የተገለጠ ነው።»

(ሕጉ) ቃሉ፤ የክርስቶስ ምሳሌ ነው።
ዮሐ. 1፡1፣ 14 «በመጀመሪያ ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ... ቃልም ሥጋ ሆነ።
ሮሜ 10፡4 «የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነውና።»

ለ. መና ያለበት የወርቅ መሶብ፣ (ዘጸ. 16፡31-36)

ይህ መና፣ በየዕለቱ ለእስራኤል ልጆች ይዘንብ ከነበረው መና፣ እግዚአብሔር ለልጅ ልጅ መታሰቢያ እንዲሆን በታቦቱ ውስጥ እንዲቀመጥ ያዘዘው ሲሆን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወት እንጀራ መሆኑን የሚያሳስብ ነው። «የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምን ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም» (ዮሐ. 6፣35)።

«የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ ሞቱም ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው። ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ ሰው ከዚህ እንጀራ በበላ ለዘላለም ይኖራል እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው» (ዮሐ. 6፣48-51)።

ሐ. የበቀለች የአሮን በትር፡ -(ዘኍ. 17፡1-11)

ቆሬ፣ ዳታንና አቤሮን በሙሴና በአሮን ላይ በተነሡ ጊዜ እግዚአብሔር ተቃዋሚዎቹን ቀስፎ፣ እርሱ የመረጠው ካህን አሮን መሆኑን ለእስራኤል ሁሉ የገለጸበት መንገድ ነው። 12ቱም ነገዶች ደረቅ በትር እንዲያመጡና በመገናኛው ድንኳን እንዲያኖራቸው ለሙሴ ይነግረዋል።
(ዘኍ.17፡5)፤ እንዲህም ይሆናል የመረጥሁት ሰው በትር ታቆጠ ቁጣለች በእናንተም ላይ የሚያጉረመርሙባችሁን የእስራኤልን ማጉረምረም ከእኔ ዘንድ አጠፋለሁ።»
«እንዲህ ሆነ፤ በነጋው ሙሴ ወደ ምስክሩ ድንኳን ውስጥ ገባ እነሆም ለሌዊ ቤት የሆነች የአሮን በትር አቆጠቆጠች ለመለመችም፣ አበባም አወጣች፤ የበሰለ ለውዝም አፈራች» (በአንድ ቀን ውስጥ፤ ዘኍልቁ 17፣8)።

ይህች የለመለመችና ያፈራች የአሮን በትር ለዘላለም ሊቀ ካህናችን የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ታመለክታለች።

ኢሳ. 53፡2 «በፊቱ እንደ ቡቃያ ከደረቅም መሬት እንደ ሥር አድጓል፤ መልክና ውበት የለውም ባየነውም ጊዜ እንወድደው ዘንድ ደም ግባት የለውም።»

ዕብ. 8፡1-2 «ከተናገርነውም ዋና ነገሩ ይህ ነው፤ በሰማያት በግርማው ዙፋን ቀኝ የተቀመጠ እንዲህ ያለ ሊቀ ካህናት አለን። እርሱም የመቅደስና የእውነተኛይቱ ድንኳን አገልጋይ ነው።»

7. <u>የሥርየቱ መክደኛ</u>፡ - (ዘጸ. 25፡17-22፤ 37፡6-9)

ይህ ዕቃ ሙሉ በሙሉ ከጥሩ ወርቅ የተሠራ የታቦት መክደኛ ነበረ። እግዚአብሔር በዚህ ሥርየት መክደኛ ላይ ሆኖ ሙሴን እንደሚያነጋግረው ይነግረዋል። የእግዚአብሔር ድምጽ፣ የእግዚአብሔር ክብርና ግርማ ያለበት ሥፍራ ነበረ።

የሥርየቱ መክደኛ የእግዚአብሔርን መገኘት ያሳያል፣... በምሥክሩ ታቦት ላይ ባለው በሁለት ኪሩቤል መካከል <u>በስርየት መክደኛው ላይ ሆኜ አነጋግርሃለሁ</u>» (ዘጸ. 25፡22)። ስለ ኪሩቤል የሚናገሩ ተጨማሪ ጥቅሶች 2ነገ. 19፣15፣ 1ሳሙ. 4፡4 ሕዝ. 10፤ መዝ. 80፡1፣ 99፡1 ስሙ እንደሚገልጸው፤ ይህ «የስርየት መክደኛ» እግዚአብሔር፤ ሕዝቡ በካህኑ በኩል ያቀረቡትን የደም መሥዋዕት አይቶ ሥርየትን (ይቅርታን) የሚያደርግበት ቦታ ነው። በአሁኑም ዘመን እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ምክንያት ምህረትን የሚሰጥበት የፀጋ ዙፋን እንዳለ ቃሉ ይነግረናል። «እንግዲህ ምህረትን (ሥርየትን) እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ።» ዕብ. 4፡16

## የካህናቱ ልብስ ( ዘጸ. 28 እና 29)

በመገናኛው ድንኳን ውስጥ የሚያገለግሉ ካህናት፣ በተለይ ሊቀካህኑ የሚለብሰውን ልብስ አሠራርና ዓላማ በዘጸአት ምዕራፍ 28 እና 29 እናነባለን።

የሚለበሱት ነገሮች ሰባት ልዩ ልዩ ነገሮች እንደሆኑ እናያለን። በዘጸ. 28፡4 ላይ «የሚሠሩአቸውም ልብሶች እነዚህ ናቸው <u>የደረት ኪስ</u> <u>ኤፉድም ቀሚስም</u> <u>ዝንጕርጕር ሸሚዝም መጠምጠሚያም መታጠቂያም</u> እነዚህም ካህናት ይሆኑልኝ ዘንድ ለወንድምህ ለአሮን ለልጆቹም የተቀደሰ ልብስ ያድርጉ» በማለት ስድስቱ ሲጠቀሱ፤

በዘጸ.28፡42፡ ደግሞ አንደኛው ተጠቅሷል «ኃፍረተ ሥጋቸዉንም ይከድኑበት ዘንድ የበፍታ ሱሪ (ቁምጣ) ታደርግላቸዋለህ ከወገባቸዉም እስከ ጭኖቸው ይደርሳል፡፡»

**በዘጸ.28፡36-37 በመጠምጠሚያው (በቆቡ) ላይ «ቅድስና ለእግዚአብሔር» የሚል የወርቅ ቅጠል ምስል አለበት**

**ይህ የሊቀ ካህኑና የካህናቱ ልብስ «ለክብርና ለጌጥ» እንደሆነ በዘጸ. 28፡3-ና 40 እናነባለን፡፡ ይህም የሚያሳየን በእግዚአብሔር መቅደስ ውስጥ ማገልገል (ክብርና ጌጥ) እንደሆነ ነው፡፡ «የሚያከብሩኝን አከብራለሁ» እንዳለ ሁሉ፤ እኛ እግዚአብሔርን በምናከብርበት ጊዜ እርሱ ደግሞ በክብርና በውበት ያስጌጠናል፡፡**

**ሌላው የሚያሳየው፤ በአዲስ ኪዳን ያለን አማኞች ሁሉ ካህናት እንደመሆናችን መጠን (1ጴጥ. 2፡9፤ ራዕ. 1፡6) ክብራችንና ጌጣችን ነውና ኢየሱስ ክርስቶስን መልበስ እንዳለብን ነው ገላ. 3፡27፡፡**

**የእነዚህ ልብሶች አለባበስ፣ ቅደም ተከተል፡፡**

**በመጀመሪያ የበፍታ ሱሪውን (ከውስጥ የሚለበስ ቁምጣ)**
**ቀጥሎ፣ ዥንጉርጉር ሸሚዝ (ከውስጥ የሚለበስ)**
**ቀጥሎ፣ ቀሚሱን**
**ቀጥሎ፣ ኤፉዱን**
**ቀጥሎ፣ የደረቱን ኪስና መታጠቂያውን**
**ቀጥሎ መጠምጠሚያውን እና የወርቁን ቅጠል፡፡**

**እነዚህ ልብሶች በሙሉ ግልጋሎት ቢኖራቸውም ሦስቱን ብቻ እንመለከታለን፡፡**

**<u>ኤፉድ</u>፡ - (ዘጸ. 28፡6-14)**

**ይህ ልብስ ከትከሻ ጀምሮ እስከ ወገብ አካባቢ የሚደርስ ወይም ትንሽ ወረድ የሚል ከሁለት ወገን ተሠርቶ በትከሻው ላይ የተጋጠመ ከጥሩ በፍታ (ሐር) የተሠራ ነው፡፡ በወገቡም ላይ አብሮት የተጠለፈ መታጠቂያ አለው፡፡ በኤፉዱ ጫንቃ ወይም ትከሻ ላይ (በሁለቱም ትከሻዋች ላይ) ሁለት የመረግድ ድንጋዮች አሉ፡፡ በእነዚህም ሁለት ድንጋዮች ላይ እንደ አወላለዳቸው ስድስት ስድስቱ የእስራኤል ወገኖች ስም በወርቅ ፈርጥ ተቀርጾባቸዋል፡፡**

- **እነዚህን አሥራ ሁለቱን የእስራኤል ወገኖች ስም የያዙትን ሁለት ድንጋዮች ሊቀካህኑ በትከሻው ላይ (በኤፉድ ትከሻ ላይ) ተሸክሞ በእግዚአብሔር ፊት ይቀርባል፡፡**

ዘጸ. 28፥12 «የእስራኤል ልጆችም የመታሰቢያ ድንጋዮች ይሆኑ ዘንድ ሁለቱን ዕንቁዎች በኤፉዱ ጫንቃዎች ላይ ታደርጋለህ፤ አሮንም በሁለቱ ጫንቃዎች ላይ ለመታሰቢያ ስማቸውን በእግዚአብሔር ፊት ይሸከማል።»

ከኤፉድ አሠራርና አለባበስ የምንማረው የኤፉድ ዋና ዓላማ ሊቀ ካህኑ የአስራኤላውያንን ነገዶች ስም በትከሻው ላይ ተሸክሞ (ድካማቸውንና ኀጢአታቸውን ጭምር) በእግዚአብሔር ፊት እንደሚያቀርባቸው ነው።



## የሊቀ ካህኑ ልብስ

በትከሻው መሸከሙ የሚያሳየው፤ የእግዚአብሔር ኃይል ድካማችንን እንደሚሸከም ነው፡፡ በአንጻሩም፤ የአዲስ ኪዳን ሊቀካህናችን የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ስንመለከት በእግዚአብሔር ፊት ስለ እኛ እንደሚማልድ እናነባለን፣

ዕብ. 7፡23-25 «እነርሱም (የብሉይ ኪዳን ካህናት የሆኑት) ብዙ ናቸው። እርሱ (ክርስቶስ) ግን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ የማይለውጥ ክህነት አለው፤ ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራል፤ ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል።»

«በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም። ዕብ. 4፡15። «በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ <u>ሕመማችንንም ተሸክሞአል</u>» ኢሳ. 53፡4።

2. <u>የደረቱ ኪስ</u> (<u>የፍርድ የደረት ኪስ</u>) (ዘጸ. 28፡15-30)

ይህ በኤፉድ ላይ የሚደረብ መደረቢያ አንድ ስንዝር በአንድ ስንዝር የሆነ በደረት ላይ የሚንጠለጠል ኪስ ነው። እንደ ኤፉዱ አሠራር የደረቱም ኪስ ከጥሩ በፍታ የተሠራ ሲሆን፥ ከኤፉድ ትከሻ ጋር በወርቅ እንደተጎነጎነ ሆኖ በተሠራ ገመድ የተያያዘ ነው።
በዚህ በደረት ኪስ ውስጥ የሚገኙት ከአሥራ ሁለት የዕንቁ ፈርጦች የተቀረጹና የአሥራ ሁለቱን የእስራኤል ነገዶች ስሞች የያዙ አሥራ ሁለት የዕንቁ ድንጋዮች ናቸው። በተጨማሪም ካህኑ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚጠይቅበት ኡሪምና ቱሚም በውስጡ ይገኛሉ (ዘኍ. 27፣21፤ 1ሳሙ. 28፣6) ። እነዚህም አሥራ ሁለት የተለያዩ ዕንቁዎች በፍርዱ ደረት ኪስ ውስጥ ወደጎን አራት አራት ወደታች ደግሞ ሦስት ሦስት ሆነው የተደረጉ ናቸው። የዚህ የደረት ኪስ ዓላማ ምን እንደሆነ ዘጸ. 28፡29-30 ይነግረናል፤ «አሮንም ወደ መቅደስ በገባ ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ለዘላለም መታሰቢያ የእስራኤልን ልጆች ስሞች በፍርዱ ደረት ኪስ ውስጥ <u>በልቡ</u> ላይ ይሸከም። ... <u>በእግዚአብሔር ፊት ሁልጊዜ</u> የእስራኤልን ልጆች ፍርድ በልቡ ላይ ይሸከም።»
ካህኑ አሥራ ሁለቱን የእስራኤል ነገዶች እንደገና በእግዚአብሔር ፊት ተሸክሞ ሲቀርብ እናያለን።

ይህም የሚያሳየው ሊቀ ካህናችን የሆነው ጌታችን ኢየሰሱ ክርስቶስ እኛን ልጆቹን በልቡ ላይ ተሸክሞን በእግዚአብሔር ፊት እንደሚያቀርበን ነው። ልቡ የሚያመለክተው ፍቅርን ነው። ሊቀካህን የፍቅር ሰው መሆን እንዳለበት እናያለን። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውንም ፍቅር ያመለክታል።
ሊቀ ካህናችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ያህል እንደሚወደን የሚያመለክት ምሳሌ ነው።
«እርሱ ስለእኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና በዚህ ፍቅርን አውቀናል» (1ዮሐ. 3፣16)።
«ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከማኖት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር

ለማኸም የለወም (ዮሐ.15፡ 13)።»

በሊቀ ካህኑ ደረት ላይ አሥራ ሁለቱን የእስራኤል ነገዶች የሚወክሉት አሥራ ሁለት የዕንቁ ድንጋዮች፥ እያንዳንዳችን ለጌታ ዕንቁዎች እንደሆንን ያስታውሱናል።

3. <u>መጠምጠሚያው ላይ ያለው የወርቅ ምስል፡</u> -(ዘጸ. 28፣36-38)

ይህ በመጠምጠሚያው ላይ ያለው የወርቅ ምስል እንደ ቅጠል ሆኖ የተሠራ የወርቅ ምልክት ሲሆን በላዩ ላይ «ቅድስና ለእግዚአብሔር» የሚል ጽሑፍ አለበት። የዚህ የወርቅ ቅጠል ዓላማ ምን እንደሆነ ቁ. 38 ይነግረናል። «አሮንም የእስራኤል ልጆች በሚያቀርቡትና በሚቀድሱት <u>በቅዱስ ስጦታቸው ሁሉ ላይ ያለውን ኃጢአት ይሸከም፤</u> በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ (ተቀባይነት) እንዲሆንላቸው ቅጠል የሚመስለው ምልክቱ ሁልጊዜ በግምባሩ ላይ ይሁን።»

- ይህንን «ቅድስና ለእግዚአብሔር» የሚል የወርቅ ምልክት ሁልጊዜ በግምባሩ ላይ አድርጎ በእግዚአብሔር ፊት ስጦታቸውን ይዞ የሚቀርበው <u>በስጦታቸው ላይ ያለውን ኃጢአት</u> ለመሸከም እንደሆነ እናያለን።

<u>ከዚህ ክፍል የምንማራቸው ነገሮች፤</u>

ሀ. እስራኤላውያን «ቅዱስ» ብለው የሚያቀርቡት ስጦታ እንኳን በእግዚአብሔር ፊት ከኀጢአት ፍጹም ንጹህ እንዳልነበረ እኛም የምናቀርበው ቅዱስ ስጦታ (አገልግሎትና መሥዋዕት) በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም አይደለም።

<u>«በቅዱስ ስጦታቸው ላይ ያለውን ኀጢአት ይሸከም</u>»

በኢሳ 64፡ 6 «ጽድቃችንም ሁሉ የመርገም ጨርቅ ነው» ይለናል፡፡ ቅዱስና ጻድቅ ነው ብለን የምናቀርበው መሥዋዕትና ስጦታ እንኳን በእግዚአብሔር ፊት ንጹህ አይደለም፡

ለ. በቅዱስ ስጦታቸው ወይም ቅዱስ ነው ብለው በሚያቀርቡት ስጦታ ላይ ያለውን ኃጢአት በምሕረቱ አስወግዶ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ የእግዚአብሔር ቅድስና ምልክት ነው።

የእነርሱ ኃጢአት በእግዚአብሔር ምሕረትና ቅድስና ይሸፈናል፡፡ «ዓለም ሳይፈጠር <u>በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን</u> በፍቅር እንሆን ዘንድ <u>በክርስቶስ</u> መረጠን» (ኤፌ.1÷4)፡፡ የተመረጥነው (የተቀደስነው) በክርስቶስ (በሊቀ ካህናችን) እንጂ በእኛ ቅድስና አይደለም፡፡

… በክርስቶስ ኢየሱስ ለተቀደሱት … ቅዱሳን ለመሆን ለተጠሩት» (1ቆሮ. 1፤2)፡፡

«… ኢየሱስ ክርስቶስ … ቅድስና ሆነልን» (1ቆሮ. 1፡31)፡፡

<u>ከላይ የተጠቀሱትን ሦስት ልብሶችና ምሳሌነታቸውን ስንመለከት፤</u>

1. በኤፉድ፡ - በትከሻው ላይ የእስራኤልን ወገኖች ይሸከማል፡፡

   ትከሻ - የኃይል ምልክት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ኃይል የእግዚአብሔርን ሕዝብ መሸከምና መታገስ እንደሚችል ያመለክታል፡፡

2. የደረቱ ኪስ (የፍርድ የደረት) ኪስ፡ -
   በልቡ ላይ የእስራኤልን ወገኖች ስም እንዲሸከም፡ -
   ልብ የፍቅር ምልክት ነው፡፡
   «ፍቅር የኃጢአትን ብዛት (ፍርድን) ይሸፍናል፡፡»
   እግዚአብሔር በፍቅሩ ኃጢአታችንን ይቅር እንደሚል፡፡

3. የወርቁ ምልክት

   <u>የእግዚአብሔር ቅድስና</u>- በግንባሩ ላይ «ቅድስና ለእግዚአብሔር» የሚል ምልክት ያደርጋል፡፡ በሕዝቡ መስዋዕት ላይ ያለው ኃጢአት በእግዚአብሔር ቅድስና ይሸፈናል፡፡

## <u>የመገናኛው ድንኳን ሥራ መስተጓጎል</u> (ዘጸ. 32-34)

ይህንን ክፍል በምናይበት ጊዜ በጣም የሚያሳዝን ታሪክን እናነባለን፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ሁለት እንደ ጨለማና ብርሃን ተቃራኒ የሆኑ ሁኔታዎችን እንመለከታለን፡፡

1. ሙሴ በሲና ተራራ ላይ ለ40 ቀን ምንም ሳይበላና ሳይጠጣ ከእግዚአብሔር የመገናኛውን ድንኳን አሠራር መመሪያ ከማስጠንቀቂያ ጋር ይቀበላል፡፡ በተጨማሪም እግዚአብሔር የምስክሩን ጽላቶች ይሰጠዋል፡፡

■ በአጭሩ እግዚአብሔር በእስራኤላውያን መካከል ማደሪያውን ለመትከል ስለፈለገ የማደሪያውን ንድፍ ለሙሴ ይሰጠዋል፡፡

2. በአንጻሩ ደግሞ እስራኤላውን በመካከላቸው ለማደር እስከ መፈለግ ድረስ ያከበራቸውን አምላክ (ዘጸ. 32፡1-6) ረስተው አሮንን «በፊታችን የሚሄዱ አማልክት ስራልን» ሲሉት እናያለን፡፡ አሮንም ይህን ክፉ ሐሳብ ሳይቃወም በሕዝቡ ግፊት በመመራት አንድ የወርቅ ጥጃ ሠርቶ «እስራኤል ሆይ እነዚህ ከግብጽ ምድር ያወጡህ አማልክትህ ናቸው» ይላል፡፡

ሁለቱን ድርጊቶች ስናስተያይ፤ እግዚአብሔር በጣም የከበረን ነገር እያዘጋጀላቸው ሳለ ሕዝቡና አሮን ግን ከግብጽ ምድር ያወጣቸውን አምላክ በመርሳት ጣዖትን ሠርተው ሲያመልኩ እናያለን፡፡ በተለይ አሮንን ስንመለከት እግዚአብሔር በወርቅና በዕንቁ የተንቆጠቆጠ «ለክብርና ለጌጥ» ዘጸ. 28፣2 የሆነ የክህነት ልብስ እያዘጋጀለት እርሱ የውርደትን ሥራ ይሠራል፡፡

እግዚአብሔር ለእኛም የሚሰጠን ማስጠንቀቂያ አለ፤ «... ብትመለስ እመልስሃለሁ በፊቴም ትቆማለህ፣ የከበረውን ከተዋረደው ብትለይ እንደ አፌ ትሆናለህ» ኤር.15፣19፡፡ በኤር.18፣9-10 ደግሞ፣ እኛ የማይገባን ሆነን ከተገኘን እግዚአብሔርን ሊያደርግልን ከነበረው መልካም ነገር እንደሚጸጸት ይናገራል «ተመዘንክ ቀለህም ተገኘህ» ከመባል እግዚአብሔር ይጠብቀን፡፡

በዘጸ. 32፣31-32 ላይ ሙሴ ስለ ሕዝቡ አስደናቂ ምልጃ ያቀርባል፤ «ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ÷ ወዮ! እነሆ ሕዝብ ታላቅ ኃጢአት ሰርተዋል÷ ለራሳቸውም የወርቅ አማልክት አድርገዋል፤ አሁን ይህን ኃጢአታቸውን ይቅር በላቸው፤ ያለዚያ ከጻፍኸው መጽሐፍህ እባክህ ደምስሰኝ አለ፡፡» ምልጃ፤ ጥፋትን ወደ ምሕረት÷ ሞትን ወደ ሕይወት ይለውጣል፡፡

## የመገናኛው ድንኳን ሥራ መፈጸም (ዘጸ. 35-40)

ሙሴ ስለ አሮንና ስለ ሕዝቡ ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት ከማለደ በኋላ በምዕ. 35 ላይ ሕዝቡ ለመገናኛው ድንኳንና አገልግሎት የሚሆን ስጦታ በፈቃዳቸው እንዲያመጡ ያሳስባል፡፡ በምዕ. 35 እና 36 ሰዎች ያላቸውን ንብረት እና ራሳቸውንም ጭምር ለመገናኛው

ድንኳን ሥራ ሲሰጡ ይታያል፡፡ ከዚህ የምንማረው፣ አንድ ራእይ ከእግዚአብሔር ከሆነና «በተራራው ላይ እንዳሳየን ምሳሌ» ለመሥራት ከተጠነቀቅን እግዚአብሔር ያንን ራእይ ከዳር የምናደርስበትን ገንዘብም ሆነ ማንኛውንም ነገር እንዲሁም ያንን ራእይ የሚደግፉ ሰዎችን ያነሳሳል፡፡ የእግዚአብሔር ሥራ ብቻችንን የምንሰራው ሥራ አይደለም፡፡ «ለመቅደስም ማገልገያ ሥራ ሁሉ ያደርጉ ዘንድ እንዲያውቁ እግዚአብሔር ጥበብንና ማስተዋልን የሰጣቸው ባስልኤልና ኤልያብ በልባቸው ጥበበኞች ሁሉ እግዚአብሔር እንዳዘዘው ነገር ሁሉ አደረጉ» (ዘጸ. 36÷1)፡፡
ዘጸ. 36÷3-7 ያለውን ስንመለከት፣ ሕዝቡ ከሚገባው በላይ ስላመጡ ሙሴ «ከዚህ የበለጠ የሚያመጣ አይኑር» ብለ ሲከለክላቸው እናነባለን፡፡

<u>የመገናኛው ድንኳንና ዕቃዎቹ በሙሉ ተሠርተው ካለቁ በኋላ፤</u>

1. ሙሴ ማደሪያውንና በውስጡ ያለውን ሁሉ በዘይት ይቀባል (ዘጸ. 40÷9-10)፡፡ መቀባት ለእግዚአብሔር የመቀደስ ወይም የመለየት ምልክት ስለሆነ ማደሪያውና በውስጡ ያለው ዕቃ ሁሉ ለእግዚአብሔር እንደተቀደሰ ያሳያል፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ዳግመኛ የተወለደ አማኝ ሁሉ በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር መንፈስ ማደሪያ (ቤተ መቅደስ) እንደሆነ የእግዚአብሔር ቃል ይነግረናል (1ቆሮ. 3÷16፤ 6÷19-20)፡፡ በተጨማሪም ይህንን፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ማደሪያ የሆነውን ሰውነታችንን በቅድስና እንድንጠብቅ ያሳስበናል (ሮሜ 12÷1)፡፡

2. ሙሴ ሁሉንም ነገር እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ፡፡ በዘጸ. 40 ወስጥ ስምንት ጊዜ «እግዚአብሔር እንዳዘዘው» የሚሉ ቃላትን እናገኛለን፡፡

3. ሙሴ ሥራውን ሁሉ <u>እንደታዘዘው ከፈጸመ በኋላ</u> የእግዚአብሔር የክብር ደመና የመገናኛውን ድንኳን ከደን (ዘጸ. 40÷33-35)፡፡ «...እንዲሁም ሙሴ ሥራውን ፈጸመ፡፡ ደመናውም የመገናኛውን ድንኳን ከደነ÷ ... የእግዚአብሔርም ክብር ማደሪያውን ስለሞላ ሙሴ ወደ መገናኛው ድንኳን ይገባ ዘንድ አልቻለም» (ቁ. 35)፡፡

   የእግዚአብሔር ክብር እንዲገለጥ የሰው ድርሻ እንዳለ ያሳየናል፡፡ እኛ የታዘዝነውን ስንፈጽም እግዚአብሔር ክብሩን ይገልጻል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት፣ ጥያቄዎች

1. ዘጸአት በስንት ክፍሎች ይከፈላል? ምን ምን ናቸው?
2. በዘጸአት ውስጥ የሚገኙ የሚከተሉት ሰዎችና ነገሮች የምን ምሳሌዎች ናቸው?

   ሀ. ግብጽ ለ. ፈርዖን ሐ. ቀይ ባህር መ. ውሃ ያፈለቀው ዓለት ሠ. ሙሴ

3. ለእስራኤላውያን የተሰጠው ሕግ በስንት ክፍል ይከፈላል? ክፍሎቹ ምን ምን ናቸው?

4. ሕጉ የተሰጠበትን ሦስት ምክንያቶች ግለጽ፡፡

5. አስርቱ ቃላትን በሙሉ የሚያጠቃልል የአዲስ ኪዳን ትእዛዝ ምንድ ነው?
6. የመገናኛው ድንኳን በስንት ክፍል ይከፈላል? ልዩነታቸውስ ምንነው?
7. በመገናኛው ድንኳን ውስጥ የነበሩትን ሰባት ዕቃዎችን ተግባራቸውን እንዲሁም በየትኛው ክፍል እንደ ነበሩ ግለጽ፡፡
8. በኪዳኑ ታቦት ውስጥ የነበሩት ዕቃዎች ምን ምን ናቸው?
9. ሊቀ ካህኑ የእስራኤላውያንን የነገድ ስሞች የትና እንዴት ይሸከም ነበር?
10. በመጠምጠሚያው ላይ ያለው የወርቅ ምስል ምን የሚል ነበር? ዓላማውስ ምንድን ነበር?